# እናስተዋውቃችሁ



ፓስተር አለማየሁ ደምሴ

እናስተዋውቃችሁ

# ናትናኤል

ናትናኤል በገሊላ ውስጥ የምትገኘው ቃና ተወላጅ ነው። ናትናኤል የፊልጶስ ጓደኛ ነበር። እንደ ማንኛውም እስራኤላዊ በጊዜው የነበረውን የሄሮድስ መንግሥት ገልብጦ፥ የሮማውያንን ጦር ሠራዊት አባሮ በማስወጣት ፍትሕና ሰላም የሠፈነበት መንግሥት የሚያቋቁመውን የመሲሁን መምጣት የሚጠባበቅ ሰው ነበር።

ፊልጶስ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ከሆነ በኋላ ወደ ጓደኛው ወደ ናትናኤል ሄዶ መሲሁን ያገኘው መሆኑን ይነግረዋል። ናትናኤል የሰማው ዜና ደስ አሰኘው። የበለጠ የመስማት ፍላጎት አደረበት። ነገር ግን ሌላም ጥያቄ ሳይጠይቅ ፊልጶስ በመቀጠል የመሲሁን ማንነት ነገረው። "ኢየሱስ ይባላል፥ የናዝሬት ሰው ነው። አንተ ከምትኖርበት ከቃና አጠገብ ማለት ነው። የናዝሬቱን አናጢ ዮሴፍን ታውቀው የለም? ኢየሱስ የሱ ልጅ ነው። (ዮሐ. 1፥45) ናትናኤል ይህን ሲሰማ ኩምሽሽ አለ። "በል ተወው በርግጥ ዮሴፍ የታወቀ አናጢ ነው። ነገር ግን የፖለቲካ ሰው አይደለም። ኢየሱስ ቢሆንም የአናጢ ልጅ ስለሆነ ምን ትምህርት አለውና ከመንግሥት ጋር ምን ግንኙነት አለውና ነው ለሕዝቡ ትልቅ ነገር የሚሠራው?" ብሎ ሳይጠይቅ አልቀረም። ስለዚህ በመጠራጠር "ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላል?" ብሎ ጠየቀ። ናዝሬት የታወቀች ዝነኛ ሥፍራ አልነበረችም። በትናንሽ ከተሞች መካከል መቀናናትና መናናቅ ያለ ነው። በናትናኤል አነጋገር ናዝሬት ምንም ዓይነት መልካም ነገር ሊገኝባት የማትችል ሥፍራ ነች። ፊልጶስ ግን አልተከራከረውም። "ለምን አንተ ራስህ መጥተህ አታይም?" አለው እንጂ።

ናትናኤል ጥርጥሩን እንደያዘ መጣ። ቢሆንም ለማየት ነው፡መጣው። በክርክር አምነው ክርስትናን የተቀበሉ ሰዎች ቁጥር ብዙ አይደለም። ክርክር አብዛኛውን ጊዜ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። ለአንድ ሰው የክርስቶስን የበላይነት ለማሳመን ብቸኛው መንገድ ያ ሰው ከክርስቶስ ጋር እንዲገናኝ ማድረግ ነው። ብዙዎችን ለክርስቶስ የማረከው ከክርክር ይልቅ የመስቀሉ ታሪክ ነው።

ናትናኤል ወደ ኢየሱስ መጣ። ኢየሱስም፥ "ተንኰል የሌለበት በእውነት የእሥራኤል ሰው እነሆ አለ ።ናትናኤል"በኢየሱስ አነጋገር ተደነቀ። ምክንያቱም አንድ ሰው ሌላውን ሰው በደንብ ሳያውቀው እንዴት ስለ እርሱ ይህን የመሰለ አስተያየት መስጠት ይችላል? ብሎ ስላሰበ ነው። ስለዚህ ናትናኤል ኢየሱስ እንዴት ይህን ያህል ሊያውቀው እንደቻለ ለመረዳት ስለፈለገ ከወዴት ታውቀኛለህ? ብሎ ጠየቀ "በፊት፤ ከበለስህ በታች ተቀምጠህ ሳለህ አየሁህ።" አለው። ለአይሁድ የበለስ ዛፍ የሰላም ምልክት ነው። በአይሁዶች አመለካከት አንድ ሰው ከራሱ በለስና ከራሱ ወይን በታች ማንም ሳይረብሸው ከተቀመጠ ያ የሰላም ምልክት ነው (1ኛ ነገ. 4፥ 25፤ ሚክ. 4፥4)። ከዚህም በተጨማሪ ከበለስ በታች ተቀምጦ የጥሞና ጊዜ ማሳለፍብ የተለመደ ነገር ነበር። ናትናኤልም ከበለስ በታች ተቀምጦ ይህን ያደርግ እንደነበረ መገመት አያስቸግርም።

ኢየሱስ የናትናኤልን ስም ከሌሎች ጠይቆ ሊያውቅ ይችላል። ስለዚህ ስሙን ቢሆን ኖሮ የነገረው ምንም አያስደንቀውም ነበር። ነገር ግን ከዚህ የበለጠ ያውቀው ነበር። ጌታ ሁሉን ያውቃል። ዐይኖቹ ከዚህ ከሚታየው ውጫዊ አካላችን ጠልቀው ያያሉ። ናትናኤል ከበለስ በታች ተቀምጦ በተመስጦ የሚያስበውን ኢየሱስ ያውቅ ነበር። ናትናኤል ልበ ንጹህ ሰው ነበር። ንጹሕና ቅን ሰው ነበረ። እግዚአብሔር የሰው መነሻ ሃሳብ ጉዳይ ይገደዋል። የምናደርገውን ብቻ ሳይሆን ለምን እንደምናደርገው ይገደዋል። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እኔ ሰው እንደሚያይ አላይም ይላል እግዚአብሔር የሚለው። ሰው ፊትን ያያል እግዘብሔር ግን ልብን ያያል። የሰው ልብ ተንኰለኛ ነው ማንስ ያውቀዋል? ሲልም እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ የልብ አዋቂ መናገሩ ነው።

ናትናኤል ኢየሱስ ተራ ሰው አለመሆኑን ተመለከተ። ከዚህም የተነሣ መምህር ሆይ፥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፣ አንተ የእሥራኤል ንጉሥ ነህ አለው (ቁ. 49) ኢየሱስም መልሶ ከበለስ በታች አየሁህ ስላልሁህ አመንህን? ከዚህም የሚበልጥ ነገር ታያለህ አለው።

ከዚህም የሚበልጥ ነገር ታያለህ። ናትናኤል ምን የሚበልጡ ነገሮች አየ? እነዚህ ያያቸው ነገሮች ሕይወቱን ምን ያህል ለወጡት? በተወለደበት ከተማ በቃና ከተደረገው ከመጀመሪያው ተአምር ጀምሮ እስከ እውሮች ብርሀንን ማየት፣ ሽባዎች መዝለል፣ ልባቸው የተሠበረ መጠገን፣ የሙታን ሕይወትን ማግኘት ድረስ የኢየሱስን ታላላቅ ሥራዎች በገሊላና ይሁዳ ተመለከተ።

ናትናኤል የአሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት እድገት አየ። በእያንዳንዱ ቀን እያንዳንዳቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ ሲሄዱ ተመለከተ። ሰዎች ከጌታ ጋር እውነተኛ ሕብረት ሲፈጥሩ ሕይወታቸው ሲለወጥ አየ። ኢየሱስን ጌታ ብለው የሚጠሩት ቀጥር ያለመቋረጥ እየጨመረ ሲሄድ ተመለከተ። የእግዚአብሔር መንግሥት በተሰበከበት ሁሉ በገሊላ፣ በይሁዳ፣ በሰማርያና በሮማውያን ግዛት ሁሉ ከፍተኛ ተአምር ሆነ። አለማወቅ፥ ጥላቻና ክፋት የመሳሰለው መሰናክል ቢኖርም ወንጌል ተሰበከ፥ የሰዎችም ሕይወት ተለወጠ (የሠይጣን አሽክላ ተሠባበረ)።

ክርስቶስ ተራ ሰዎችን፥ እንደ ናትናኤል ያሉ ተጠራጣሪ ሰዎችን ወስዶ ታላቅና በመንፈስ

የተሞሉ ብርቱ ሰዎችና ዓለምን የሚገለባብጡ ሰዎች አደረጋቸው። ዛሬም ጌታ ይህን ተአምር ይሠራል። ዛሬም በወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ይህን ይሠራል። ራሳችንን ለእርሱ ከሰጠን ዛሬም ተራ የሆነውን ችሎታችንን ፍሬያማ ችሎታና መክሊት ያደርገዋል። ተራ የሆነው ነገር በእርሱ እጅ ሲገባ የተቀደሰ ይሆናል።

ናትናኤል ጌታ ታላቅና አስደናቂ ነገሮች ሲሰራ አየ። በሽተኞች ሲፈወሱ አየ። የኢየሱስ ደቀ መዛሙር ት በየግል ሲያድገና ቁጥራቸው ሲጨምር ተመለከተ። ከዚህም በተጨማሪ ናትናኤል ለደቀ መዝሙርነት አስፈላጊ፣ የሆነውን መንገድ አየ፥ እነዚህም እምነትና እውነተኛነት ናቸው። ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ሲያምን ከተጠራጣሪነት ድርጊትና ኃይል ወዳለበት ሕይወት ተለወጠ። ተጠራጣሪነት የበለጠ ነገር እንዳናይ እንቅፋት ይሆንብናል። ጥርጥር ይህ አይሆንም አይደረግም ይላል። ናትናኤል ከናዝሬት መልካም ነገር አይወጣም እንዳለው።
እምነት ግን ተስፋ አይቆርጥም።

ናትናኤል ክርስቶስን ለመከተል ለጥሪው ምላሽ መስጠት እንደሚያስፈልግ አየ። ከዚህም በላይ ራሱን ማታለል እንደሌለበትና እውነተኛ መሆን የሚያስከትለውን ችግርና ሃሴት ለመቀበል ፈቃደኛ ሆነ። ከደቀመዛሙር ሁሉ (ከመጀመሪያዎቹ ከ12ቱ ማለት ነው) በከፍተኛ ጭካኔ የተገደለው ናትናኤል ነው። የሚያሰቃዩት ሰዎች አሥረው በቢላ ቆዳውን ከገፈፉት በኋላ ሰውነቱ በሙሉ በደም ተነክሮ ሰቅለው እስኪሞት ድረስ አሰቃዩት። ነገር ግን ያ ለናትናኤል የመጨረሻው አልነበረም። ሞት በዚህ ሕይወት ካየው የበለጠ እንደሚያይ ቃል ከገባለት ከክርስቶስ ጋር ዘላለማዊ ሕይወት ለመኖር መግቢያ በር ነበር።

አንዲት ትንሽ ልጅ አንድ ያልተለመደ በሽታ ይዟት ትሰቃይ ነበር። ሐኪሙ የሌላ ሰው ደም ካልተሰጣት በስተቀር እንደምትሞት ተናገረ። የሚሰጣት ደም ከራሷ ደም ጋር አንድ አይነት የሆነና ደም ሰጪውም ከዚህ በፊት ተመሳሳይ በሽታ ይዞት የዳነ መሆን ነበረበት። ለዚህም የተገኘው የራሷ ወንድም ሆነ። ሐኪሙ ለዚያ ትንሽ ልጅ እህቱ ከእርሱ ደም ተወስዶ ካልተሰጣት በስተቀር የምትሞት መሆኑን ከገለጸላት በኋላ ለእህቱ ደሙን ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነ ጠየቀው።

ልጁም ትንሽ ካመነታ በኋላ በመጨረሻ እህቱ በህይወት እንድትኖር ደሙን ለመስጠት ያለውን ፈቃደኝነት ገለጸ። የደም ማዘዋወሩ ሥራ ተጀምሮ በመሃሉ ዶክተሩ እንዴት ነው ማሙሽ ብሎ ቢጠይቀው፥ "ደህና ነኝ ነገር ግን መቼ ነው ምሞተው ዶክተር?" ብሎ ሐኪሙን ጠየቀው ዶክተሩም ወዲያው ልጁ በመጀመሪያደሙን ለእህቱ ለመስጠት በተጠየቀ ጊዜ ለምን እንዳመነታ ገባው።

ልጁም ምንም እንኳን የራሱን ሕይወት ቢያጣም የእህቱን ሕይወት ለማዳን ያለውን ደም በሙሉ ለመስጠት ዝግጁ ነበር። እኛስ እንደ ናትናኤልና እንደ ትንሹ ልጅ ነን? እነርሱ ሕይወታቸውን እስኪሰጡ ድረስ ታማኞች (እውነተኞች ) ነበሩ።

ክርስቶስ ራሱን ለኛ ስጥቷል። ዛሬም ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለእርሱና ለመንግሥቱ እንድንሰጥ ይጠራናል፥ ምክንያቱም ደቀመዝሙርነት ይህን ዓይነት መሰጠት ይጠይቃል። እኛንም ከናትናኤልና ከትንሹ ልጅ ያነሰ መሰጠት አይጠብቅብንም። ይህን የመሰለው ደቀመዝሙርነት ችግርና ስቃይ ሊያስከትልብን ይችላል ነገር ግን እኛም እንደ ናትናኤል ከዚህም የበለጠ እናያለን። የበለጠ ለማየት የበለጠ የተሰጠን እንሁን። ተራውን ሕይወታችን ወስዶ በውበት፥ በሃሴትና በድንቅ የሚያንፀባርቅ ያደርገዋል።

እናስተዋውቃችሁ

# ስምዖን ጴጥሮስ (አለቱ)

ስምዖን በገሊላ ሃይቅ ዳርቻ ከምትገኝ ቤተሳይዳ ከምትባል መንደር የተወለደ አሳ አጥማጅ ነበር። ስምዖን የእንድርያስ ታናሽ ወንድም ሲሆን ፥አፈ ታሪክ እንደሚለው በአካሉ ግዙፍ ሰው ነበር።

ስምዖን ባለትዳር ነበር ። ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ለማሙዋላት ራሱን የሰጠ ፣ሃላፊነት የሚሸከም ሰው እንደሆነ ለመገመት እንችላለን። አሁንም አፈታሪክ እንደሚለው ስምዖን አንድ ወንድና አንድ ሴት ልጅ ነበሩት።ሴቷ ልጁ ሸባ ነበረች ይባላል።

እንደማንኛውም የአገሩ ሰዎች የሮማውያን አገዛዝ የሠራዊቱን ደሞዝ ለመክፈል በሚያደርገው ከፍተኛ ታክስ ፣ ጩካኞቹ ቀረጥ ሰብሳቢዎች (ቀራጮች) የሚያስከትሉት ችግር የሚሰማው ሰው ነበር።

ታድያ አንድ ቀን ታላቅ ወንድሙ እንድርያስ ወደ ቤቱ መጥቶ መሲሁን ያገኘው መሆኑን አወጀለት። ስለዚህ ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ብዙ ተነጋግረዋል። ስምዖን አየሱስ ስለሰራቸው ስራዎች ሰምቷል።ነገር ግን ከናዝሬት የሆነ ያልተማረ አናጢ ነው አየተባለ ሲወራ ስለሰማ ነገሩን ቁም ነገር ሰጥቶ አላየውም ነበር።

ናዝሬት ደግሞ ከቤተሳይዳ የማትሻል መንደር ነበረች። በመጨረሻ ስምዖን ከወንድሙ ጋር ለመሄድና ይህንን አዲስ መምህር ለመገናኘት ተስማማ (ፈቃደኛ ሆነ።)

ስምዖንና ኢየሱስ በተገናኙ ጊዜ በመጀመሪያ የተናገረው ኢየሱስ ነበር።" አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፣ ስላንተ ብዙ ነገር ሰምቻለሁ። ከዛሬ ጀምሮ ጴጥሮስ (አለት) ብዬ እጠራሃለሁ።" ዮሐ.1፡42

ስምዖን ማለት ተለዋዋጭ ፣ዋዣቂ ማለት ሲሆን አዲስ የተሰጠው ሥም ግን ጸንቶ የሚቆም አለት ማለት ነው። (ስምዖን በውስጡኒ ምን ዓይነት ቀልድ ነው? ሳይል የቀረ አይመስልም። ወንጌሎች በጴጥሮስየተሞሉ ናቸው ማለት ይቻላል። ከጌታችን ሥም ቀጥሎ በአራቱም ወንጌሎች አንደ ጴጥሮስ ሥም የተደጋገመ ሥም አይገኝም።ጌታችንም የጴጥሮስን ያህል ደጋግሞ የተናገረው ደቀ መዝሙር አይገኝም። አንዳንዴ ሲወቅሰው ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያመሰግነው እናያለን። የጴጥሮስንያህል በጌታ አጥብቆ የተገሰጸም የለም።እንደ ጴጥሮስም ጌታውን ለመገሰጽ የደፈረ የለም። (ማርቆስ8፡32)

ጌታን በድፍረት ጌታ መሆኑን የመሰከረና ጌታ መሆኑን ደጋግሞ የገለጸ፣ጌትነቱን ያወቀና ያበረታታው እንደ ጴጥሮስ ማንም የለም። ደጋግሞ ጣልቃ እየገባ ጌታን የተፈታተነም እንደ እርሱ አይገኝም። ጌታ የጴጥሮስን ያህል ጎሽ ያለውና ያመሰገነው ፥የባረከው ደቀ መዝሙር የለም። የዚያኑ ያህል ደግሞ ከአስራ ሁለቱ መካከል ይሁዳን ሳይጨምር የጴጥሮስን ያህል ከባድ ቃላት የተናገረው ሰውም አልነበረም።ከደቀ መዛሙርቱ መካከል እንደ ጴጥሮስ አዘውትሮ የሚናገር አልታየም ።

*ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ።ሉቃስ5፤8
*እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? ማቴ 19፡27
*አይሁንብህ ጌታ ሆይ ከቶ አይድረስብህ። ማቴ 16፡22
*ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንህ በውሃው ላይ ወዳንተ እንድመጣ እዘዘኝ።ማቴ 14፡28
*ጌታ ሆይ አድነኝ። ማቴ 14፡30
*አቤቱ ሕዝቡ ያስጨንቁሃልና ይጋፋህማል የዳሰሰኝ ማነው ትላለህን? ሉቃስ 8፡45
*ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ።ዮሐንስ6፡68
አንተ ክርስቶስ የሕያው የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።ማቴ.16፡16
*አቤቱ በዚህ መሆን ለኛ መልካም ነውና አንድ ላንተ፣ አንድም ለሙሴ ፣አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶችን እንስራ።ሉቃስ9፡33
*ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜ ነውን?ማቴ18፡21
*ሁሉም ቢሰናከሉ እኔ ግን ከቶ አልሰናከልም።ማቴ26፡33
*ካንተ ጋር መሞት እንካ የሚያስፈልገኝ ቢሆን ከቶ አልክድህም።ማቴ 26፡35
*የኔን እግር ለዘላለም አታጥብም።ዮሐ13፡8
ጌታ ሆይ እጄንና ራሴንደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም።ዮህንስ 13፡9
*ሰውዬውን አላውቀውም። ማቴ 26፡72
*ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ ። እንድወድህ አንተ ታውቃለህ።ዮሐንስ 21፡16።

እነዚህ የጴጥሮስን ማንነት የሚያሳዩን ነገሮች ናቸው።ጴጥሮስ ችኩል ፥ ከሁሉ ቀደም ቀደም የሚል ፥ ጣልቃ ገብ፥ሐጢአቱን ለመናዘዝ ዝግጁ የሆነ፥ ዋኝቶ ሊወጣው የማይችለው ጥልቅ ውሃ ውስጥ ሚገባ፥እንደ ትንሽ ልጅ ቶሎ ቶሎ ወደ ጌታው የሚመለስ ፣ የተሰማውን ሁሉ በቃለት ወይም በድርጊት የሚገልጽ ሰው ነበር።

ምንም እንኳን ስምዖን ስሜቱ ተለዋዋጭ ቢሆንም ተወዳጅ ሰው ነበር። የሁሉ ወዳጅ ስለነበረና ተወዳጅ ሰለነበረ ሰዎች በቀላሉ ይከተሉት ነበር።ከዚህ የተነሳ ከኢየሱስ ቀጥሎ የደቀ መዛሙርት መሪ ነበረ ለማለት ይቻላል።

አዲስ ኪዳን ጴጥሮስ ከደቀ መዛሙርት ሁሉ ተቀዳሚ ስፍራ እንደነበረው ያሳየናል። እንዲያ

ውም ጴጥሮስ በተነሳበት ስፍራ ሁሉ የሁሉ መሪ እንደነበረ ማየት ይቻላል። ጴጥሮስ ከሌሎቹ የተለዩ ባህርያት ነበሩት። በራሱ የሚተማመንና የሚያደርገውን ሁሉ በከፍተኛ መሰጠት የሚያደርግ ሰው ነበር።

የስምዖን ጴጥሮስ መጠራትና መለወጥ እውነተኛ የተፈጥሮ ባህሪውን አላጠፋውም።ጌታ ባይማልድለትና ባይጸልይለት ኖሮ ጭኩ ልነቱ አጥፍቶት ነበር። ነገር ግን ደረጃ በደረጃ በጌታው ትምሕርት ፥በጌታው ምሣሌነትና ጌታ በሰጠው ስልጣና የረጋ አለት አደረገው። ጴጥሮስ ብዙ ጊዜ ቢደናቀፍና ቢወድቅም፥ ለጌታው ያለው ጽኑ ፍቅርና አምልኮ መልሶ አስተካክሎ አቆመው።

ከጌታው ጋር በነበረባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ጴጥሮስ ገና ያልበሰለና በቅጡ ያልተገራ ነበር። የጴጥሮስ መገራት እርሱንምሆነ ጌታውን ያስከፈለው ዋጋ ቀላል አልነበረም።

ጴጥሮስን ስለ ችኩልነቱና ስላልጠራ ባህርዩ የፈለግነውን ያህል ብንወቅሰውም ልበ ቀዝቃዛ አልነበረም። ልቡ ለጌታ ሁልጊዜ የጋለ ነበር። በልቡ ያለውን ለመናገር ሁልጊዜ ቀዳሚ የሆነውን ያህል ፥በኋላ ሕይወቱንም ለመስጠት አላንገራገረም። ጴጥሮስ በዚህ ትልቅ ምሳሌ ሆኖልናል። ከልበ ቀዝቃዛነት፥ ከግዴለሽነትና በርቀት ከመከተል እግዚአብሔር ይጠብቀን።

ጴጥሮስ ኃጢአተኛነቱ በጣም የሚሰማው ሰው ነበር። በዚህ ጴጥሮስ መንፈሱ የተሰበረና የለሰለሰ ልብ ያለው መሆኑን እንረዳለን።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት እንደተመለከትነው ጴጥሮስ ብቻ ነበር ኃጢአቱን ያስታወሰው።"ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ።" ጌታም አትፍራ አለው።የእውነተኛ መንፈሳዊ ሰው እውነተኛ ምልክት ይህ ነው።

በመንፈሳዊ ሕይወቱም ሆነ በስጋው መበልጸጉ ያለፈውን ኃጢአቱን ሲያስታውሰውና የማይገባኝ ነኝ ሲል ፤ እንደ ኃጢአቴ አላደረገብኝም እንደ በደሌም አልከፈለኝም ማለቱ የመንፈሳዊነቱ ፈርጥ ነው።ጴጥሮስንና ይሁዳን ስናወዳድር ፥ በኋላ ሰባኪ የሆነው ጴጥሮስ ጌታን አላውቀውም ብሎ ክዶ ነበር። ነገር ግን ሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጴጥሮስን በመድረክ ላይ ይሁዳን ግን ራሱን በገመድ አንጠልጥሎ እናያቸዋለን።

አሁን ጴጥሮስ የሚያውቀው የጸጋ ባለዕዳ መሆኑን ብቻ ነው። ንስሐ የሚያመጣውን መዳንና እረፍት ስለሚያውቅ ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም እንዲሰረይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ አላቸው።

በጰንጠቆስጤ ቀን መንፈስ ቅዱስ ያንን ግዙፉን ጴጥሮስን ሁለንተናውን ሞላው። ዕውነትም አሁን አለት ሆነ። ፈሪሳውያንንም ሆነ ሕዝቡን አልፈራም ። የምስራቹን አወጀ። ከዚያ በኋላ ምንም ስህተት ሰርቶ ቢያውቅና ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ግጭት ቢፈጥርም ክርስቶስን በመስበክና በድፍረት ምሳሌያቸው ሆነ። በመጨረሻም አፈ ታሪክ እንደሚለው ጴጥሮስ ወደ ሮም ሄዶ በዚያ ሰማዕት ሆነ።ሮማውያን ሊሰቅሉት በተዘጋጁም ጊዜ "አባካችሁ እኔ እንደ ጌታዬ ለመሞት ብቃት የለኝምና ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ።" ብሎ በለመነው መሠረት እግሮቹን ወደ ላይ ራሱን ወደ ምድር ዘቅዝቀው በመስቀል ገደሉት : :

## እኔና ጌታዬ

አሳ ካሰግር ወጥቼ
ጎህ ሲቀድ ጠዋት ተነስቼ
ስታገል ዋልኩኝ በርትቼ

ቁጭ ብዬ ሳለሁ ደክሜ
ከተፍ አለና ወንድሜ
ከአጥማጁ ጋራ አገናኘኝ
አጥማጁም እኔን አጠመደኝ

አሳ አጥማጅ የነበርኩትን
ታጠምዳለህ አለኝ ሰውን
መረብ አልባ ነው ማጥመዴ
በማፍቀርና መውደዴ
ስለ አጥማጄ ታሪክ በመንገር
ለእርሱ ነፍሳትን በማስገር

ለሶስት ዓመታት አስተማረኝ
አጠማመዱን አሳየኝ
የርሱ ማጥመጃ ፍቅር
አውተብትቦ የሚያስቀር

ጎሮሮን አንቆ ሳያደማ
በመልካም ለዛው እያስማማ
የታመመ አካል ፈውሶ
ነፍስን ከእሳት መልሶ

እኔ እሻል ፥ እኔ እበልጥን ይጠላል
ከፍ ሚል ዝቅ ይበል ይላል
እርሱም ዝቅ ብሎ እግር ያጥባል
አንሶ መብለጥን ያስተምራል

ካጠመደኝ ብዙ ተምሬ
ከርሱ ጋራ አብሬ ኖሬ
ሌሎች ቢክዱህ እኔ አለሁ በማለት
ቆሜ ፎክሬ

የቁርጥ ቀን የመጣ እለት
ሶስቴ ካድኩት በአንድ ሌሊት
ጭራሽ ተስፋ ቆረጥኩና
የሰጠኝን ስራ ተውኩና
ጉዋደኞቼን ጠራሁና
ወደ ጀልባዬ ተመለስኩ
አሳ አገኝ ብዬ ደከምኩ
እኔ ክጀው ያልካደኝ
ለዘላለሙ የወደደኝ
ቁርሴን በወጉ መገበና
ዳግም ፍቅሩን ገለጸና
"ትወደኛለህ ?' አለኝ ከቶ የማያልቅ ይመስል
እረኛ አደርገኝ ቁጭ አለ እኔ ይጠላኛል ስል።

# ያዕቆብና ዮሐንስ

ያእቆብና ዮሐንስ የሰሎሜ ልጆች ናቸው። (ማር.15፥40፣ማር.16፥1፣) በዮሐንስ 19፥25 እንደተገለጸው ሰሎሜ የኢየሱስ እናት ማርያም እህት እንደነበረች በብዛት ይታመናል። ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ይልቅ ዮሐንስና ጌታ ኢየሱስ የተቀራረቡበት ምክንያት የስጋ ዝምድናቸውም ሊሆን ይችላል።

አባታቸው ዘብዴዎስ (ማቴ. 4፥21) በገሊላ ወንዝ አሳ አስጋሪ ነበር። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ሲጠራቸው ንግዳቸውን ለአባታቸው ትተው ነበር የተከተሉት። ይህ ቤተሰብ በኢኮኖሚ አቋሙ ጠንከር ያለ ነበር ለማለት ይቻላል። ለዚህም መረጃ የሚሆኑን፥

1. አሽከሮች ነበሯቸው። (ማር 1፥20)
2. ሰሎሜ የጌታን አገልግሎት በገንዘብ ይረዱ ከነበሩት ሴቶች መካከል ተጠርታለች። (ማር. 1፥20)
3. ጌታ ሊቀበር ሲል አካሉን ለመቀባት ሽቱና ቅመማ ቅመም አምጥታለች።

ያእቆብና ዮሐንስ የተወለዱት ጴጥሮስ፣ እንድርያስና ፊልጶስ ከተወለዱባት ከቤተሳይዳ ነበር። ያእቆብ ከሐዋርአት መካከል የመጀመሪያው ሰማዕት ሲሆን በ44ዓ.ም. በሄሮድስ አግሪጳ ተገድሏል። እነዚህ ወንድማማቾች እንደ ሌሎች ብዙዎች ሁሉ የጌታ ኢየሱስ ተልዕኮ በጊዜው በሃገራቸው ላይ በስልጣን ላይ የነበረውን የሮማ መንግሥት አፍርሶ በምትኩ የመንገስ ጉዳይ መስሏቸው ነበር። ያእቆብና ዮሐንስም በዚህ "አብዮታዊ መንግሥት " ውስጥ ስለሚኖራቸው የስልጣን ድርሻ ለመወያየት ወደ ጌታ ዘንድ መጥተው ነበር። በርግጥ ጌታ የሚያካሂደው አብዮት ነበር። ነገር ግን በአመፅና በጦር መሳሪያ ሳይሆን በፍቅር ነበር እንጂ።

በማርቆስ 10፥35 እንደተገለጸው "መምህር ሆይ የምንለምንህን ሁሉ እንድታደርግልን እንፈልጋለን " ይሉታል ። ጌታም "ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላችሁ" ባላቸው ጊዜ "በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝህ አንዳችን በግራህ መቀመጥን ስጠን" አሉት። በዘመናችን አነጋገር አንዳችንን ጠቅላይ ሚኒስትር አንዳችንን ደግሞ መከላከያ ሚኒስትር አድርገን ብሎ እንደመጠየቅ ነው።

ይህ ጥያቄአቸው ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት ምን ያህል እንዳስቆጣቸው ለመገመት አያዳግትም። "ድፍረታቸውን ታያላችሁ፣ ከማን ተሸለው ነው? " (ማር. 10፥41)።ጌታ ግን በዚህ ጊዜ በአጠገቡ የነበሩትን አሥራ ሁለቱን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ደቀ መዛሙርቱ ለሆንነው ሁሉ አጋጣሚውን በመጠቀም እጅግ አስፈላጊ የሆነ መመሪያ አስተላለፈ።

"እንዲሁም ከመካከላችሁ የበላይ ለመሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ መሆን አለበት...። " በጌታ መንገድ ከፍ ማለት የሚገኘው ዝቅ በማለት ብቻ ነው። የጌታ አገልጋይ መሆን ማለት ወዶ ባርያ መሆን ማለት ሲሆን፤ አንዱ ለሌላው ወዶ በፍቅር የሚገዛበት ሁኔታ ነው። ከዚህ መመሪያ ባገኙት እውቀት ሊሆን ይችላል ያዕቆብና ዮሐንስ የስቃይንና ያገልግሎትን ጽዋ የጠጡት ። ስለ ክርስቶስ ሞትን እንኳ ሊጋፈጡ የሚችሉበትን ጸጋ አገኙ።

እነዚህ ደቀ መዛሙርት ይህንን በጠየቁበት ጊዜ የሚፈልጉትን ለማግኘት ባላቸው ጽኑ ፍላጎት የሚነዱና ያልበሰሉ ወጣቶች  ነበሩ። ከጌታ ጋር በቆዩና ከእርሱ በተማሩ ቁጥር ግን የነበራቸው ሰብዕና እያደገ መሄዱን እናያለን።ዮሀንስ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ የቅርብ ጓደኛ እንደነበረና እስከ ሞት ድረስ ያልተለየው እንደነበረ እንመለከታለን።ዮሐንስ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ዕለት ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሲደበቁና ሲበተኑ መግባት እስከሚችልበት ስፍራ ድረስ ጌታን በእስሩ ወቅት ተከትሎ ተጉዟል ። ከጲላጦስ የፍርድ አዳራሽ ጀምሮ እስከ ቀራንዮ ኮረብታ ድረስ ከኢየሱስ ጋር ነበር። በዚያም ከኢየሱስ እናት ከማርያም ጋር ሊያጽናናት ከጎኗ ነበር ። በዚሁ ስፍራ በልቧ ውስጥ ሰይፍ ያለፈውን እናቱን ይጠብቅለት ዘንድ ከጌታ አደራን ተቀበለ።

ያእቆብና ዮሐንስ በባህሪያቸው ቁጡዎች ነበሩ። ከዚህም የተነሳ ጌታ ወልደ ነጎድጓድ የሚል ቅጽል ሥም ሰጣቸው።ያዕቆብና ዮሐንስ ምናልባት ሰዎች ሲቃወሙአቸው ፊታቸው ሲለዋወጥ ጌታ ብዙ ጊዜ ተመልክቶ ይሆናል ይህንን ስም የሰጣቸው። ትዕግስት የሌላቸው ቁጡዎች ነበሩ። አንድ የተሳሳተ ነገር ሲያዩ ቶሎ የሚቆጡና የሚገነፍሉ ሰዎች ነበሩ።

በሉቃስ 9፥51-56 እንደምንመለከተው የሰማሪያ ሰዎች ማረፊያ ስለከለከሏቸው እሳት ከሰማይ አውርደን እንድናጠፋቸው ፍቀድልን የሚል ጥያቄ አቅርበው በጌታ ስለ ስህተታቸው ተገስጸዋል። ጌታ ደቀ መዛሙርቱ ሲያደርጋቸው ቁጡዎች መሆናቸህውን ያውቅ ነበር። ነገር ግን እነዚህ የነጎድጓድ ልጆች ቀስ በቀስ ቁጣቸውን መቆጣጠር ተማሩ።ግባቸው ተስተካከለ። ነፍስና መንፈሳቸው ተፈውሶ ሕኢወታቸው ተለወጠ። እርሱን ለመታዘዝ ራሳቸውን ለፈቃዱ አስገዙ። በተለይም ዮሐንስ የፍቅር ሐዋርያ ሆነ።

ይሁዳ ከመካከከላቸው ተስቶ በወጣበት "የመጨረሻው ራት " በመባል በሚታወቀው የፋሲካን ራት አብረው በበሉበት ቀን "እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።" (ዮሐንስ 13፥35) አላቸው።

ይህንን አዲስ ትእዛዝ አሥራ አንዱም ደቀ መዛሙርት ሰምተዋል። ነገር ግን በዮሐንስ ልብ የተዘራው ዘር መቶ እጥፍ አፍርቷል ማለት እንችላለን። ሐዋርያው ዮሐንስ እጅግ ሽምግሎ ወጣቶች ለአምልኮ ወደ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሲያመጡት "ልጆቼ ሆይ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ እያለ ይመክራቸው እንደነበር ይተረካል። ለምን ሁልጊዜ ይህንን እንደሚላቸው ጠይቀውት ሲመልስ "ምክንያቱም ይህ የጌታ ዋና ትዕዛዝ ነው። ሁላችንም ይህን ብንፈጽም ከዚህ የበለጠ አያስፈልግም ። ፍቅር የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ነውና።" በማለት ኢመልስላቸው ነበር ይባላል። የወልደ ነጎድጓድ የፍቅር ሐዋርያነት ፣ የያእቆብ ከሐዋርያት መካከል ቀዳሚ ሰማዕት መሆን ምን ያህል አስገራሚ ነገር ነው። ጌታ ድንቅ ሥራውን በሕይወታቸው እንደሰራና ፍሬውም ምን ያህል ያማረ እንደነበረ ለማየት ያስችላል።

ከኢየሱስ የተማረ እርሱን ይመስላል ። ኢየሱስ ፍቅር ነው። ሕይወቱን መስዋዕት አደረገ። የርሱን መንገድ መከተል የሚወድ ሁሉ እርሱ ራሱ እንደተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።

እ ና ስ ተ ዋ ው ቃ ች ሁ

# ፊልጶስ

ፊልጶስ የቤተሳይዳ ተወላጅ ነበር። ከዚች አነስተኛ የአሣ አጥማጆች ከተማ አምስተኛው ደቀ መዝሙር መሆኑ ነው። ቤተሳይዳ ለዚያ ዘመን እንኳን ትንሽ ከተማነበረች ። ነገር ግን ከእርሷ ምኩራብ የሰውን ልጅ ታሪክ ሂደት የለወጡ አምስት (ከ12ቱ) ተገኙ።

የዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ ፊልጶስን እንዳገኘው ይነግረናል ( ዮሐ.1፥43)። ፊልጶስ ኢየሱስን ፍለጋ አልመጣም፤ ለሁለቱ መገናኘት ጀማሪው ኢየሱስ ነው። ፊልጶስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስማቸው ተደጋግሞ ከተጠቀሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር።(ዮሐ 6፥5፣12፥21፤14፥8) ። ፊልጶስ ረጋ ያለና ሰላማዊ ሰው ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ዋጋ ያለውና ጠቃሚ ሰው መሆኑን አየ ። ስለዚህም አገኘውና ደቀ መዝሙር እንዲሆን ጋበዘው።

ፊልጶስ አዲስ አማኝ ቢሆንም ውጤት ያለው ምስክር ነበር። ራሱ እንዳመነ (እንደተለወጠ) ወዲያው ናትናኤልን ወደ ክርስቶስ አመጣው (ዮሐ1፥40-46)። ናትናኤል ኢየሱስን ለመቀበል ዝግጁ አልነበረም።"የናዝሬቱ ኢየሱስ " የሚለውን መጠሪያ ንቆታል። ነገር ግን ፊልጶስ መከራከር ኢየሱስ መሲህ ለመሆኑ የማያጠራጥር ማረጋገጫ ለማቅረብ አልሞከረም፤" መጥተህ እይ " ብሎ ጋበዘው።

የፊልጶስ አባባል ቀጥሎ ያለውን የሚመስል ነው ። "እኔ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን አምናለሁ። ከና ዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን ? ላልከው ልልህ የምችለው ነገር ቢኖር ራስህ መጥተህ ተመልከት ብቻ ነው።" ናትናኤል በርግጥ መጣ። በርግጥም አየ። እርሱም ጌታን "ጌታ" ብለው ከጠሩት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ሆነ።

ለፋሲካ በአል ከግሪክ መጥተው የነበሩት ሰዎች ኢየሱስን ለማየት በፈለጉ ጊዜ በመጀመሪያ ያናገሩት ፊልጶስን ነበር ።ይህ ምናልባት ፊልጶስ ከአሥራ አንዱ ይልቅ ለእንግዳ ሰው ለማናገር የሚቀል እንደሆነ ሊያሳይ ይችላል (ዮሐ12፥20-22) ።

ኢየሱስ የሦስት አመታት አገልግሎቱን ከሰጠ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ከኢየሱስ ጋር የፋሲካን በአል ለማክበር ተሰብስበው ነበር። ጌታ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ስለ አብ በተናገረ ጊዜ ፊልጶስ "ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል" ብሎ ጠየቀ (ዮሐ 14፥8-9)።ኢየሱስም መለስ ብሎ " እስካሁን ከናን ጋር ኖሬ የዚህን ጥያቄ መልስ አታውቅም? እኔን አይተህኝ ከሆነ ፣ አብን አይተሃል። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። አብ በእኔ ውስጥ ነው እኔም በእርሱ ውስጥ ነኝ። እኔና አብ አንድ ነን።" አለው።

ፊልጶስ ከዚህ በፊት እንደዚህ አስቦ አያውቅም ነበር ወይም እንደዚህ አይመስለውም ነበር። ደቀ መዛሙርቱም ይህን እውነት አልተረዱም ነበር።ኢየሱስን ማየት እግዚአብሔርን ማየት እንደ ሆነ።ጌታ ኢየሱስ ለሽበዎች <ለእውሮች፣ ልባቸው ለተሰበረ፣ ለድሆች የነበረውን ፍቅርና ርኅራኄ አይቷል፤ በዚህም ያየው እግዚአብሔርን ራሱን መሆኑን መገንዘብ ጀመረ።

ከፊልጶስ ጥያቄ የተነሳ የእግዚአብሔር ንፍቅር፣ምሕረት፣ፍትሕ፣ይቅርታና ጽድቅ ለመረዳት ኢየሱስን መረዳት እንዳለብን እንገነዘባለን። ዛሬ ዓለም አብን አሳዩኝ፣እግዚአብሔርን አሳዩኝ ምን ይመስላል?ብላ ትጠይቃለች። ለዚህ መልሱ ኢየሱስን ተመልከቺ ነው።

ስለ ፊልጶስ የምናውቀው ይኸው ነው።አነስተኛ ከሆነችና ካልታወቀች መንደር የተገኘ ቀንና ሌሊት አሳ ከምትሸት መንደር የወጣ ሰው ነው። አፈ ታሪክ እንደሚለው የፊልጶስ ሥራው ጋሪና ሠረገላ መጠገን (ማደስ) ነበር። ፊልጶስ ከሌሎቹ ደቀ መዛሙርት የላቀ ሆኖ አይታይም። ለማወቅ የሚጠይቅ አእምሮ ያለውና ለክርስቶስ የተሰጠ ሰው ነበር፤በጎና ታማኝ ተከታይ መሆኑን አስመስክሯል። ስለ ደቀ መዛሙርቱ የምናጠናው ጥናት ሌላ ምንም ውጠየት ባይኖረው እንኳን ክርስቶስ ማንኛውም ዓይነት ችሎታ ያለውን ሰውእንዴት ሊጠቀምበት እንደሚችል ማወቃችን ይበቃል። ኢሱስ ፊልጶስን ወስዶ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ አድርጎ ለታላቅ ሥራ ሊመርጠው ቻለ። ለክርስቶስ የማያስፈልግ ሰው የለም።

ዛሬም ክርስቶስ ፊልጶስን እንደፈለገ ይፈልገናል።በመጀመሪያ ልዩ ወዳጃችን ሊሆን ይፈልጋል። ከእርሱ ጋር እንድንኖርና ለእርሱ እንድንኖር፣እንድንከተለው ይጠራናል።ማንነታችን አይገደውም።በውስጣችን የተደበቀውን ችሎታ ወይም መክሊት እንድናዳብረው ይረዳናል። ባስቸጋሪ ወቅቶችና በማይመቹ ሰዓቶች ከኛ ጋር ይሆናል። በድላችንና በደስታችን ጊዜ አብሮን ደስ ይለዋል ። ልንከተለው (ደቀ መዝሙሩ ልንሆን) ከመረጥን ዓላማና ትርጉም ያለው ሕይወት እንድንኖር ይመራናል። አሁንም ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ፊልጶስ በሚሲዮናዊነት ወደ ፍርግያ ሄዶ ሲሰብክ ሄርፒሊስ በተባለ ሥፍራ በስቅላት እንደተገደለ እንረዳለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ የተተረከ ከኢትዮጵያ ጋር ግንኙነት ያለው ታሪክ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በፊልጶስ ታዛኝነት ተከናውኗል። (የሐዋሪያት ሥራ 8፥26-40)።

የፊልጶስ ታሪክ ዛሬም እኔና እርስዎ የጌታን ዘላለማዊ ዓላማ በመታዘዝ እስከ መጨረሻው ጌታ ብቻ የሚያውቀውን አገልግሎት እያገለገልን እንድንኖር ያበረታታናል።

እ ና ስ ተ ዋ ው ቃ ች ሁ

# ቶማስ

ማቴዎስ እንደሚናገረው ቶማስ 7ኛው ደቀ መዝሙር ነው (ማቴ.10፥3) ። መንትያም በመባል ይታወቃል (ዲዲሞስ ማለት መንትያ ማለት ነው ። (ዮሐ.11፥16) ። ነገር ግን የማን መንትያ እንደሆነ አይታወቅም። በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ዝርዝሩ የቀረበው (የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ዝርዝር ) በጥንድ በጥንድ ሆኖ ቶማስ የተጠቀሰው ከቀራጩ ማቴዎስ ጋር ነው። አፈ ታሪክ እንደሚለው ቶማስ አናጢ ነበር።

ቶማስ ፊቱ ጭፍግግ ያለና ሁሌ ያዘነ የሚመስል እንደሆነ ይነገራል። ቶማሰ ተጠራጣሪ ሰው ነበር ። ስለ ድርጊቶች መረጃ የሚፈልግ (የሚጠይቅ ) ሰው ስለሆነ ጥሩ ጠበቃ ይወጣው ነበር ይባላል። ቶማስ ብዙ የሚናገር ሰው አልነበረም።ለመጀመሪያ ጊዜ ሲናገር የምንሰማው የጌታ ኢየሱስ ምድራዊ ህይወት ማብቂያ ሳምንት ላይ ነበር። አልአዛር በቢታንያ ለሞት በሚያደርስ ህመም ታሞ ነበር። ጌታም ወዳጁ አልአዛር መታመሙን ሲሰማ ደቀመዛሙርቱን ተመልሰን ወደ ይሁዳ እንሂድ አላቸው። "መምህር ሆይ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር፥ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን?" አሉት። ቶማስ ጌታው በቀጥታ ወደ ጥፋት እንደሚሄድ ስላሰበ ጨርሶ ተስፋ በመቁረጥ አነጋገር ለሌሎቹ ደቀ መዛሙርት "ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ" አላቸው።

ቶማስ በልቡ ጌታው ከይሁዳ በህይወት እንደማይመለስ ርግጠኛ ነበር። ቶማስ ጌታውን ከህይወቱ የበለጠ ስለሚወደው ከእርሱ ጋር ለመሞት የወሰነ ይመስላል። ቶማስ በህይወት እምብዛም ተስፋ የማያደርግ ፥ ተስፋ ያደርግ የነበረው ነገር እየደበዘዘ የመጣበት ሰው ነው። የቶማስ አነጋገር ተስፋ የመቁረጥ አነጋገር ነበር። ተስፋ ያደረግሁት ነገር ካልተሳካ መኖር ምን ይረባኛል? ሞቼ ባርፈው ይሻለኛል ያለ ይመስላል።

ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ጌታ እስራኤልን ይቤዣል ብለው ተስፋ ጥለውበት ነበር። ያም ሳይሆን መዘግቱ ልባቸውን አውኮት ነበር። ከዚህም የተነሳ የተሌኤዩ ጥያቄዎች ይጠይቁ ነበር። ሞት የሚጠብቀው መሆኑን ሲረዱ ደግሞ ቃል የገባላቸው መንግሰት መቅረቱ እንደሆነ ገመቱ። ታዲያ ቶማስ ደግሞ እንዲያው በተፈጥሮውም የከፋው ስለነበረ ይሄ ሁሉ ሲጨማመርበት ጨርሶ ተስፋ ቆረጠ።

ቶማስ ለሁለተኛ ጊዜ ሲናገር የምንሰማው ጌታ ኢየሱስ አልፎ ሊሰጥ በነበረበት ምሽት ከደቀመዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን ራት ባደረገበት ወቅት ነበር። (ዮሃ.14፥1-4) ጌታ ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ "...ወደምሄድበት ታውቃላቸሁ ፥መንገዱንም ታውቃላችሁ " ብሎ በተናገረ ጊዜ ቶማስ "ምን ማለቱ ነው? ለምን በግልፅ አይናገርም!" ያለ ይመስላል። ሌሎቹም ተመሳሳይ ጥያቄ ሳይፈጠርባቸው አይቀርም። ቶማስ ጌታ ያለውን በደንብ መረዳት ስለነበረበት ጥያቄ ጠየቀ። " ጌታ ሆይ ወደምትሄድበት አናውቅም። እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን ? " አለው። ቶማስ በደንብ ሳይገባው የሚያምን ሰው አልነበረም ። ነገርን ከስሩ ማወቅ ይፈልጋል።

ቶማስ በዚህ ጥያቄው ጌታ ወርቃማ የሆነውን እውነት እንዲናገር ረድቶአል፤' እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ( ዮሀ.14፥6)የቶማስ ጥያቄ ለኛም ጠቅሞናል። እኛም የህይወትን መንገድ ማወቅ እንፈልጋለን ። ዛሬ ብዙ መንገዶች እንዳሉ እንሰማለን። "ይህን መንገድ ተከተሉ ፥ ያኛውን መንገድ ያዙ" የሚሉ ድምፆች እንሰማለን። ዛሬም ቢሆን "መንገ ዱን እንዴት እናውቃለን የሚለው ጥያቄ የዘመኑ ሰው ጥያቄ ነው። ኢየሱስ ለቶማሰ "እኔ መንገድ ነኝ" ብሎ መለሰለት።

ዛሬም ለዘመኑ ሰው ከዚህ የተለየ ወይም ከዚህ የተሻለ መልስ የለም።

*አንድ ብቻ አለ፤ አንድ ብቻ አለ*

*አንድ ብቻ መንገድ*

*እርሱም ኢየሱስ ነው*

*ወደ አብ ሚወስድ።*

በሰላም ለመኖር፥ ህብረት፣ አንድነት፣ ፍቅር ለመመስረት መልሱ ኢየሱስ ነው።ኢየሱስ ለጥያቄ ሁሉ መልስ ነው።ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሄር ጋር ሰላምን ይመሰርታል፣ ህብረት ይፈጥራል። ሰው ከእግዚአብሄር ጋር ሲታረቅ ከራሱና ከሌላውም ጋር ይታረቃል፣ሰላም ይፈጥራል።ኢየሱስ መልስ ነው።

በዚያች ምሽት ጌታ አልፎ ተሰጠ፣ ተያዘ፤ለፍርድ ቀረበ፣ ተሰቀለ፣ተቀበረ።ያ ወቅት የደቀ መዛሙርት እምነት የተፈተነበት ወቅት ነበር።በነዚያ አስከፊ ቀናት ውስጥየደቀ መዛሙርት እምነትና ተስፋ በጥርጥር ውስጥ ወደቀ። እምነታቸውና ተስፋቸው ተሰቀለ፣ሞተ፣ ተቀበረ።የተስፋም ብልጭታ አልነበራቸውም። ምክንያቱም ጌታቸው ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሳ ገና መጻህፍትን አላስተዋሉም ነበር። ነገር ግን ሞት ሊይዘው ስላልቻለ መቃብሩን ፈነቃቅሎ ወጣ።

ጌታ ሞትን ድል አድርጎ በተነሳበት ምሽት ለደቀ መዛሙርቱ ተገለጠ። በመካከላቸውም ቆሞ "ሰላም ለእናንተ ይሁን " አላቸው። (በዚያን ጊዜ ሰላም በልባቸው ፍስስ አለ።) ይህንም ብሎ እጆቹንም እግሮቹንም ጎኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱ ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው።

ቶማሰ ግን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አልነበረም ። በዚያ የከበረ የሰንበት ቀን ቶማስ የት ነበር?

# እናስተዋውቃችሁ

ለምን ከሌሎቹ ጋር አልነበረም? ወዴት እንደነበረ አናውቅም። በዚያች ቀን ከደቀ መዛሙርቱ መለየት አልነበረበትም። ቶማስን ከደቀ መዛሙርት ጋር እንዳይሆን ያደረገው ምክንያት ምንም ይሁን ምን አለመኖሩ ግን ትልቅ ጉዳት አድርሶበታል። ምክንያቱም ከሞት የተነሳውን ጌታውን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታይ አላየውም፤የመጀመሪያውንም "ሰላም ለናንተ ይሁን!" የሚለውን ቡራኬ አልተቀበለም። ቡራኬውን ማጣቱ ብቻ አይደለም፤ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሃሴት ሲያደርጉ የርሱ ልብ ግን በሀዘንና በመከፋት ተሞላ።

ቶማስ የደስታቸው ተካፋይ ሊሆን አልቻለም። ቶማሰ የኢየሱስን ከሞት መነሳት አላመነም።የነገሩትን ሊያምን አልቻለም። ይቃዣሉ አለ።አብደዋል አለ ። ትእቢት ፣ቅናት፣ የልብ መራርነት ፣ቁጣና አመጽ ሁሉ ተፈጠረበት። ጌታን አይተነዋል ባሉት ጊዜ " የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ፣ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ ፣እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም" አላቸው።

አንድ ሳምንት አለፈ። በዚህ የሳምንት ጊዜ ውስጥ ደቀ መዛሙርቱ ቶማስን ለማሳመን ያላቸውን ጥረት ሁሉ ሳያደርጉ አይቀሩም። እውነትን እንዳንቀበል ከሚያደርገን ነገር አንዱ የራሳችን ኩራት ነው። ቢሆንም ደቀ መዛሙርቱ እንደምንም ብለው በዚያች ቀን ከነርሱ ጋር እንዲቆይ ማድረግ ቻሉ።

ከሳምንት በሁዋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ቶማስ ባለበት ድንገት ተገለጠ። ቶማስ ከራሱ አፍ የወጡትን ያለማመን ቃላት ጌታ ሲደግምለት ምንኛ ራሱን ይጠላ? ከሁሉም የባሰው ደግሞ ህያው የሆነው ጌታ የቶማስን ያለማመን ቃል ለማሙዋላት ቶማስን ለማስደሰት ራሱን ትሁት ሲያደርግ ማየቱ ምንኛ ያሳፍረው። " ጌታዬና አምላኬ" ባይል ኖሮ ሀፍረትና ራሱን መኮነን ብቻ ይገለው ነበር። ቶማስ አሁን የሚያየው ህልም ወይም ቅዠት አለመሆኑን አወቀ። ኢየሱስ ህያው መሆኑን አረጋገጠ። ኢየሱስም "ቶማሰ ስላየህኝ አምነሀል ፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው ። " አለው።

ቶማስ ኢየሱስ ህያው መሆኑን ማወቁ በህይወቱ ትልቅ ለውጥ አመጣ። ከዚህ በፊት ያልተረዳው እውነት ሁሉ አሁን ይገባው ጀመር። ቶማስ እንደ ደቀ መዝሙር የምስራቹን ለሚሰሙ ሁሉ ሊናገር ወጣ። " እትጠራጠሩ የኔን ያህል ተጠራጣሪ አልነበረም፤ አሁን ግን ህያውን ጌታ አይኔ አየችው ጥርጥሬም ከኔ ጠፋ። ያመናችሁ ሁኑ እንጂ ያላመናችሁ አትሁኑ" እያለ የመሰከረ ይመስለኛል።

ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው !" አለ ጌታ። ሳያዩ የማመን ብፅእና ፤ፍቅርና ተስፋ ብርቱ በሆነበት እምነት ቀላል ነው። የምንኖርለትና ልናየው ተስፋ የምናደርገው ነገር ፣ በሙሉ ልባችን የምንወደው ነገር ፣ ቀንና ሌሊት የምንጸልይለት ነገር፣ የወደፊት ተስፋችንን የጣልንበትን ነገር ልንቀበለው ዝግጁ ነን።ቶማሰ አሁንም "ትራዲሽን" እንደሚለው በፋርስና ህንድ ውስጥ ወንጌልን ሰበከ።

በመጨረሻም "ካረማንዴል" ተብሎ በሚጠራ ደቡብ ምስራቅ ህንድ ውስጥ በቀስት እንደ ኢላማ አድርገው ከተጫወቱበት በሁዋላ በመጨረሻ በጦር ወግተው ገደሉት።

ዛሬ ከቶማስ ለራሳችን የምንማረው ምንድነው? እግዚአብሄር ራሱን በሚገልጥበት ስፍራ በዚያ ካለው ህብረት አንጥፋ።እምነታችንን ለማሳደግና ለማጠንከር ቃሉን እንመገብ። ጌታችን ህያው ነው! ከብሮአል ። እንደገና ተመልሶ ይመጣል።

"በእሳት ምንም ቢፈተን ከሚጠፋው ወርቅ ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ..." 1ኛ ጴጥሮስ1፥7

# ቀራጩ ማቴዎስ

ማቴዎስ የኖረው በገሊላ ክልል ነበር። ገሊላ በይበልጥ ገጠር ሆና ትናንሽ ከተሞችና መንደሮች ያቀፈች ክፍለ ሃገር ነበረች። አብዛኞቹ ነዋሪዎችዋ ገበሬዎችና አሳ አጥማጆች ነበሩ። ቢሆንም ኢየሱስ ከአስቆሮቱ ይሁዳ በስተቀር ደቀ መዛሙርቱን በሙሉ የመረጠው ከገሊላ ነበር። ክርስቶስ ሃይማኖታዊና ታዋቂ የነበሩትን ትቶ ተራ ሰዎችና ኃጢአተኞችን መረጠ።

ማቴዎስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል። የመጀመሪያው በማቴ.9፥9 ኢየሱስን ለመከተል ሲጠራ ነው። ከዚያም አራት ጊዜ በሐዋሪያት ዝርዝር ውስጥ (ማቴ. 10፥3፣ ማር. 3፥18 ፣ሉቃ. 6፥15 ፣ የሐዋ.1፥13) ተጠቅሷል። በማቴ.9፥9 " በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ፣ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው " የተባለውና በማርቆስ 2፥14 እና በሉቃስ 5፥27 " በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ሌዊ " የተባለው ያው አንዱ ሰው ነው። በሦስቱም ተመሳሳይ ወንጌሎች (ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ታሪኩ ይመሳሰላል። ስለዚህ ሌዊ የማቴዎስ የመጀመሪያ ስሙ ነው።

የአንድ ሰው በሁለት የተለያዩ ስሞች መጠራት በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ነበር። ያው አንዱ ሰው የዕብራይስጥ ስም ( ለምሳሌ-ሳውል) እና የግሪክ ስም ( ለምሳሌ-ጳውሎስ ) ሊኖረው ይችላል። ማቴዎስ ቀራጭ ነበር ። የራሱ ወገኖች ከሆኑት የእስራኤል ህዝብ ቀረጥ እየሰበሰበ ወደ ሮም መንግስት ካዝና የሚያስገባ፣ ከላዩም ለራሱ የሚያስቀር ሰው ነበር። ቀራጮች በአይሁድ ህብረተሰብ ዘንድ በጣም የተናቁና ማንም የማያከብራቸው እንዲያውም እስራኤልን ወርረው ከያዟት የሮም ወታደሮች የባሰ የተጠሉ ነበሩ።

እንደ ማቴዎስ ላለው አይሁዳዊ ሰው ደግሞ ቀራጭ ሆኖ መገኘት ህዝቡንና ወገኑን የከዳ፤ በአይሁድና ዘንድ የተጠላና የተተፋ መሆን ነበር። ሀይማኖቱን በተመለከተም ወደ ምኩራብ መግባት የማይችል ፣ በቤተ መቅደስ ገብቶ መስዋዕት ማቅረብና ማምለክ አይፈቀድለትም ነበር። በሉቃስ ወንጌል 18፡10-14 በሚገኘው የቀራጩና የፈሪሳዊው ጸሎት ምሳሌ ውስጥ እንደሚታየው ቀራጩ በሩቅ ቆሞ ነበር። የአህዛብን አደባባይ አልፎ ወደ መቅደሱ መግባት አይፈቀድለትም ነበር። በወንጌሎች ውስጥ ቀራጭ የሚለው ቃል ሁሌ የሚጠቀሰው ሐጢአተኞች ከሚለው ጋር ነው። ማቴዎስ በመቅረጫው ተቀምጦ ከህዝቡ ቀረጥ የሚሰበስብ ሰው ስለነበረ ያየው ሁሉ በጥላቻ የሚመለከተው ሰው ነበር፡፥ ነገር ግን ለዚህ ሐጢአተኛ አንድ አስደናቂ ነገር ሆነለት። በህብረተሰቡ ዘንድ የተጠላና የተናቀ ሆኖ ሳለ የሚወደውና የሚፈልገው አንድ ሰው ነበረ።

> ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ
> የሚባል አንድ ሰው አየና ተከተለኝ አለው። (ማቴዎስ 9፡9)

ማቴዎስ ኢየሱስ "ተከተለኝ " ሲለው አላመነታም። አሮጌውን ሕይወቱን አንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ (ኃላ ጥሎ ኢየሱስን ተከተለ። ማቴዎስ ትሁት ሰው ነበር ። ያለፈውን ሕይወቱን ለመሸፋፈን ሲሞክር አናየውም። በጻፈው ወንጌል ውስጥ የአሥራ ሁለቱን ሐዋሪያት ስም ሲዘረዝር ራሱን የጠቀሰው ቀራጩ ማቴዎስ በማለት ነው (ማቴዎስ 10፡3)።

ሌላ የማቴዎስን ትህትና የምናይበት በዚሁ ምዕራፍ 10ኛው ቁጥር ላይ የጠቀሰው ነገር አለ።

> በቤቱም ( በማቴዎስ በራሱ ቤት) በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እነሆ ብዙ ቀራጮችና
> ኃጢአተኞች መጥተው ከእየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ ።

ማቴዎስ በማዕድ የተቀመጡትን ሰዎች ማንነት ከመናገር በስተቀር ስለ ማዕዱ ትልቅነት የተናገረው ነገር የለም። ነገር ግን እርሱ ሳይጠቅስ የተወውን ሉቃስ በሚገባ ጠቅሶት እናያለን።

> ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት ፤ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው
> የነበሩ ከቀራጮችና ከሌሎች ሰዎችም ብዙ ህዝብ ነበሩ። (ሉቃስ 5፡29)

በዚህ ታላቅ ግብዣ ላይ ማቴዎስ ከኢየሱስና ከደቀመዛሙርቱ በተጨማሪ ቀራጮችና ኃጢተኞችን፣ የኅብረተሰቡ ዝቃጭ የተባሉትን ጋበዘ። ማቴዎስ ጓደኞቹና እንደ እርሱ ተናቁት ስለ ኢየሱስ እንዲሰሙ ፈለገ። እርሱ ያገኘውን መዳን ሌሎችም እንዲያገኙ።

ከወንጌሉ እንደምንረዳው ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን ጠንቅቆ ያውቃል፣ ምክንያቱም በወንጌሉ ውስጥ ከብሉይ ኪዳን ከሕግ መጻሕፍት፣ ከመዝሙር፣ ከነቢያት መጻሕፍት በአጠቃላይ ከ60 ጊዜ በላይ ጠይቋል። ማቴዎስ ቅዱሳት መጻሕፍትን በራሱ ጥረት ያጠና መሆን አለበት፣ ምክንአቱም ቀራጭ በመሆኑ ወደ ምኩራብ ሄዶ ለመማር ዕድል ነበረው ለማለት ያስቸግራል።

ማቴዎስ ስለ ኢየሱስ አስቀድሞ ብዙ ያወቀ መሆን አለበት። ተአምራት ማድረጉን፣ ደዌን መፈወሱን፣ አጋንንት ማውጣቱን፣ ኃጢአተኞችን መውደዱን ስም_ል። ስለዚህ ኢየሱስ ወደ እርሱ መጥቶ "ተከተለኝ" ሲለው ሁሉን ነገር ጥሎ ለመከተል የሚያበቃ እምነት ነበረው። እምነቱ የታየው ወዲያውኑ ኢየሱስን በመከተሉ ብቻ ሳይሆን ከኢየሱስ ጋር ከመሠረተው አዲስ ግንኙነት የተነሣ በመደሰቱ ጓደኞቹ ሁሉ ኢየሱስን እንዲያዩለትና ስለ እርሱ እንዲያውቁለት ግብዣ ማድረጉ ጭምር ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ስለ ማቴዎስ በወንጌሎች ውስጥ የተጠቀሰ ነገር የለም። እንደ ደቀመዝሙርና ሐዋሪያ ክርስቶስን ሲከተል ቆይቷል። እስከ መከራው ሰአት ድረስ አብሮት ነበር፤ የትን ሣኤው ምስክሮች ከሆኑት አንዱ ነው። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ በዚያ ነበር። በኋላም ከኢየሱስ እናት ከማርያምና ከወንድሞቹ ጋር ጌታ የገባላቸውን የተስፋ ቃል ሲጠብቅ ነበር (የሐዋ. 1፥10፣ 1፥14)

ማቴዎስ ከዚያ በኋላ ስለሠራው ስራ ያለን መረጃ የተዛባ ወይም አፈታሪካዊ ነው። አፈታሪክ እንደሚለው ማቴዎስ በአይሁድ መካከል ወንጌልን ለአሥራ አምስት አመት ከመሰበኩም ሌላ ወደ ሌላ አገር ከመሄዱ በፊት ለአይሁድ ወንጌልን ገዛ ቋንቋቸው ጽፎ ሰጥቷቸዋል። ማቴዎስ ወንጌል የሰበከባቸውን አገሮች በተመለከተ ጥንታዊ ፀሐፎዎች የሚናገሩት የተለያየ ነው። ነገር ግን ሁሉም ኢትዮጵያን ሲጠቅሱ ጥቂቶቹ ደግሞ ፔርሺያን መቆዶንያና ሦርያን ይጠቅሳሉ።

አንዳንዶች ማቴዎስ የሰማዕት ሞት አልሞተም ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሰማዕት ሆኖ ነው ያለፈው ይላሉ። ቢሆንም የት እንደተገደለና በምን ዓይነት ሞት እንደሞተ አይታወቅም።

# ቀነናዊው ስምዖን

ቀናነዊው ስምዖን የሮምን መንግስት ቅኝ አገዛዝ ለማስወገድ ይታገል የነበረው የፖለቲካ ቡድን አባል እንደነበረ ይገመታል። በሐዋሪያት የስም ዝርዝር ውስጥ ከመጠቀሱ በስተቀር ስለ እርሱ የሚታወቅ ነገር የለም። ከሐዋሪያው ጴጥሮስ (የዮና ልጅ ስምዖን) ለመለየት ሲባል ቀነናዊው ስምዖን ተብሎ ተጠርቷል (ማቴ. 10፥43፣ ማር. 3፥13) አፈ ታሪክ እንደሚለው ስምዖን ወንጌል ለመስበክ የሄደው ወደ ግብጽ አገር ነበር። ከዚያም በኋላ የአስቆሮቱ ካይደለው ይሁዳ ጋር በመተባበር ዛሬ ኢራን በመባል ከምትታወቀው የቀድሞዋ ፋርስ እና አርሜኒያ ውስጥ ወንጌል ሲሰብክ ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ወደ መካከለኛው ምሥራቅና አፍሪካ ተጉዞ እንደነበረም ይነገራል።

ስለ ቀናናዊው ስምዖን አሟሟት የምናገኘው መረጃ በጣም ይለያያል። አንዳንዶች ሰማርያ ውስጥ በስቅላት ነው የሞተው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ኢራን ውስጥ በመጋዝ ለሁለት ሰንጥቀው ነው የገደሉት ይላሉ። አሁንም ሌላ አፈ ታሪክ እንደሚያወራው ስምዖን ወደ ብሪታኒያ ተጉዞ ወንጌል ሲሰብክ የሰማዕትነት ሞት ነው የሞተው።

# ታዴዎስ

ታዴዎስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት አንዱ ነበር። ይህ ሐዋሪያ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ በመባልም እንደሚታወቅ ይታመናል (ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ለመለየት ሲባል)። በአንዳንድ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ታዴዎስ የሚለው ስም በአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ስም ዝርዝር ውስጥ ይገኛል። በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ግን በዚያ ምትክ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳየሚለው መጠሪያ ተጠቅሶ ይገኛል። በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ሁለት ወይም ሦስት የተለያዩ ስሞች ሊኖረው ይችል ነበር። እንደ የግሪክ ቋንቋ ስም እና የእብራይስጥ ቋንቋ ስም ያለ ማለት ነው። አንዳንዴም ሰዎች በሚሠሩበት ሙያ ስም ይጠሩ ነበር።

ታዴዎስ የሚለው ስም በማቴዎስ ወንጌል 10፥3 በሚገኘው የሐዋሪያት ስም ዝርዝር ውስጥ በእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብና በቀነናዊው ስምዖን መካከል ይገኛል። በማርቆስ ወንጌል 3፥18 ይኸው ስም እንደገና ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልክ ሰፍሮ ይገኛል። በሀዋሪያትሥራ 1፥13 ግን የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ የተባለው መጠሪያ ከስምዖን ቀጥሎ ነው የተጠቀሰው። በሉቃስ ወንጌል 6፥16 ደግሞ ይሁዳ (የያዕቆብ ልጅ) በአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ስም ዝርዝር ውስጥ በቀነናዊው ስምዖንና በይሁዳ አስቆሮቱ መካከል ይገኛል። በዮሐንስ ወንጌል14፥22 የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ ኢየሱስን አንድ ጥያቄ መጠየቁ ተጠቅሷል ። የሆነ ሆኖ ሁለቱ ስሞች በአንድ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ በአንድ ላይ ተጠቅሰው አይገኙም ። ይህም ሁለቱም ስሞች የአንድ ሰው የተለያዩ መጠሪያዎች ናቸው የሚለውን አሳብ ያጸናል።ከጌታ ዕርገት በኋላ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ውጭ ወንጌል ለመስበክ በመጀመሪያ ከወጡት ሐዋሪያት መካከል አንዱ ታዴዎስ መሆኑ ይነገራል።ከዚህም በተጨማሪ ታዴዎስ ለአንድ አሕዛብ ንጉስ ወንጌልን በድፍረት ከመሰከሩት ሐዋሪያት አንዱ እንደሆነ ይታመናል። ታዴዎስ ከበርጠለሜዎስ (ናትናኤል) እና ከቶማስ ጋር በመሆን በአርሜኒያ ወንጌል ሰብኳል። እንደዚሁም የቀረውን ዕድሜውን በሦሪያና በሰሜን ኢራን ወንጌል በመስበክ እንዳሳለፈና የሰማዕትነት ሞት ሞቶ ካራ ካሊስ በተባለ ሥፍራ እንደተቀበረ ይነገራል።

እ ና ስ ተ ዋ ው ቃ ች ሁ

# የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ

ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሀል ሁለቱ ያዕቆብ በሚለው መጠሪያ ይታወቃሉ። የመጀመሪያው የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ ሲሆን ሁለተኛው የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ነው ። አዲስ ኪዳን ስለ ሁለተኛው ያዕቆብ የሚሰጠን ግልጽ መረጃ የእልፍዮስ ልጅ መሆኑን ብቻ ነው (ማቴ. 10፡3፣ ማር. 3፡18፣ ሉቃ. 6፡15፣ የሐዋ. ሥራ 1፡13) ። ይህን አጋጣሚ ምክንያት በማድረግ ሁለተኛውን ያዕቆብን በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች በተመሳሳይ ስም ከተጠቀሱት አያሌ ሰዎች ጋር ለማያያዝ የተደረጉ ሙከራዎች አሉ።ከእነዚህም ሰዎች መሀል ዋነኛው " የጌታ ወንድም ያዕቆብ" ነው። ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ የጌታን ወንድም ያዕቆብን ጠቅሶታል (ገላ. 1፡19 ፣2፡9፣ 2፡12)። የጌታ ወንድም ያዕቆብ የተባለው ያዕቆብና የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ በመባል የሚታወቀው ያዕቆብ ያው አንዱ ሰው የእልፍዮሱ ልጅ ያዕቆብ ነው የሚለው አመለካከት ለረጅም አመታት ተቀባይነት አግኝቶ የቆየ ሲሆን በዘመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አመለካከት ግን ሁለት የተለያዩ ሰዎች ናቸው ።

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ማለት ታናሹ ያዕቆብ ነው የሚሉ አሉ። ታናሹ ያዕቆብ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሶስት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን ያውም ከእናቱ ጋር በተያያዘ ነው (ማቴ. 15፡40፣ ማቴ. 27፡56፣ ማር. 16፡1)። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት መካከል የዘብዴዎሱ ልጅ ያዕቆብ ስመ ጥር ከመሆኑ የተነሳ አንዳንዴ "ታላቁ ያዕቆብ ይባል ስለነበረ የእልፍዮስን ልጅ ያዕቆብን ታናሹ ያዕቆብ ነው ቢባል የሚመስል ነገር ይሆናል።

ከዚህም በተጨማሪ የእልፍዮስ እናት የማርያም ባል ቀልዮጳ ሌላው ስሙ አልፍዮስ መሆኑ በጥንት ቤተክርስቲያን ዘንድ ያገኝ ስለነበረ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ትንሹ ያዕቆብ በመባል ሲጠራ ቆይቷል ። የሐዋሪያው ማቴዎስ አባት ስም እልፍዮስ ስለሆነ ሁለተኛውን ያዕቆብንና ማቴዎስን ወንድማማች ለማድረግ የተደረገ ሙከራ አለ። የሆነ ሆኖ ሁለቱ ወንደማማች ለመሆናቸው ከአዲስ ኪዳን አንዳችም መረጃ አናገኝም።

የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ስለ ሰራው ሥራ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተጻፈ ነገር አናገኝም። አፈ ታሪክ እንደሚለው ያዕቆብ በዘጠና ስድስት አመት እድሜው የሰማዕትነት ሞት ሞቷል። በ62 ዓ.ም. አይሁድ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ወደ ታች ወርውረው ከጣሉት በኋላ በዱላ ቀጥቅጠው እንደገደሉት ይነገራል።

# እንድርያስ

## የመጀመሪያው ደቀ መዝሙር

ኢየሱስ እንዲከተሉት ከጠራቸውና ከመረጣቸው ደቀ መዛሙርት እንድርያስ የመጀመሪያው ነበር። እንድርያስ በገሊላ ሐይቅ ዳርቻ በምትገኝ ቤተ ሳይዳ በምትባል አሳ አጥማጆች የሚኖሩባት ትንሽ መንደር ውስጥ ተወለደ። እንድርያስ በአካባቢው እንደ ሚኖሩት ሰዎች አሳ በማስገር የሚተዳደር ሰው ነበር። እንድርያስ በመጀመሪያ ከዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር። መጥምቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ በሚሰብክበት ጊዜ በስብከቱ ተማ ርከው ከሚከተሉት አንዱ ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን ከዮሐንስ የሚበልጠውን አገኘ። አንድ ቀን ኢየሱስ ዮሐንስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ተሰበሰቡበት ቦታ መጣ። ኢየሱስ በአጠገባቸው ሲያልፍ ዮሐንስ አወቀና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ሲል ስለ ኢየሱስ መሰከረላቸው፥ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ፥ የዓለ ምን ኃጢአት ሁሉ የሚያስወግድ። " ይኸውላችሁ የናዝሬቱ ኢሱስ መጣ፥እርሱ ነው መቤዠትንና ደኅንነትን የሚያስገኝላችሁ ማለቱ ነበር።

በዚህ ጊዜ እንድርያስና ከዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አንድ ሌላ ሰው ከሌሎቹ ተለይተው ኢየሱስን ለመ ከተል ተነሱ። ፈጠን ባለ እርምጃ ከኋላው በመከተል ደረሱበት። ኢየሱስም የሰዎችን ኮቴ ስለሰማ ወደ ኋላው ዞሮ ሲመለከት ሁለቱን አያቸው። ወደ እርሱም ሲጠጉ " ምን ትፈልጋላችሁ ? " ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም " መምህር ሆይ የት ነው የምትኖረው ? " ብለው ጠየቁት።ኢየሱስም ሊያነጋግራቸው ስለፈለገ ሁለቱ አብረውት እንዲሄዱ ጋበዛቸው። ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ማምሻውንና ሌሊቱንም እንድርያስ ከኢየሱስ ጋር ተነጋገረ። ከዚያች ቀን ጀምሮ እንድርያስ ለኢየሱስ ተሰጠ። ሕይወቱን ሙሉ ሲፈልገው የነበረውንም አገኘ። የመጀመሪያውም የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሆነ።

ኢየሱስን በማግኘቱ በጣም ስለተደሰተ ሌሎችን ወደ ኢየሱስ ለማምጣትና ለማስተዋወቅ ተነሳ። ይህንንም በማድረግ የመጀመሪያው ወንጌላዊ ሆነ። ወንጌሎች እንድርያስ ሌሎችን ከክርስቶስ ጋር ለማስተዋወቅ ስለነበረው ፍቅር ይናገራሉ። ፍቅሩ በሌሎች ሰዎች ሕይወትውስጥ ውጤት ከማስከተሉም በላይ መሲሁን በማግኘቱ ደስ ብሎት ነበር። ደስታውም ታላቅ ስለነበረ ሌሎችም የደስታው ተካፋይ እንዲሆኑ ፈለገ። እንድርያስ የክርስትና ሕይወትን መሰረታዊ ዓላማ አሳየ። ክርስቶስን ለዓለም ማሳወቅንና መመስከርን፥ ይህን ካላደረግን እምነታችን ሙት ሆኖ ይቀራል።

እንድርያስ እሱና አይሁድ ወገኖቹ ሁሉ ሲጠብቁት የኖሩት መሲህ ኢየሱስ መሆኑን ተረዳ፥ ያገኘውን ለሌሎች ለማካፈል ፍላጎት ስለነበረው ወደ ቤቱ ተመልሶ በመሄድ ወንድሙን " መሲህን አግኝተነዋል " አለው (ዮሐ. 1፡42)። ወንድማማቾቹ ስለ እምነታቸውና የኢየሱስ መሲህነት ምን ትርጉም እንዳለው

መነጋገራቸው አያጠራጥርም።

በንግግራቸው በሙሉ እንድርያስ ኢየሱስ አዳኝ መሆኑን ተናግሯል። በመጨረሻም እንድርያስ ወንድሙን ስምዖንን ወደ ኢየሱስ ይዞት ሄደ። ከኢየሱስም ጋር አስተዋወቀው። ሰዎች ከኢየሱስ ጋር መተዋወቅ አለባቸው። የኛ ጥረት ሰዎችን ከኢየሱስ ጋር ማስተዋወቅ መሆን አለበት። ስምዖን ከኢየሱስ ጋር በመገናኘቱ ሕይወቱ መለወጡን ስናስብ እንድርያስ በወንድሙ ሕይወት ውስጥ ምን ያህል ሚና እንደተጫወተ እንረዳለን። በሃዋሪያት ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ውስጥ ስምዖን ጴጥሮስ የነበረውን ታላቅነት ስናስብ እንድርያስ ለወንድሙ ላደረገውነገር ትልቅ ዋጋ እንሰጠዋለን። እንድርያስ ለክርስቶስ የተሰጠ ባይሆን ኖሮ ስምዖን ጴጥሮስ ይኖር ነበር ?ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን።

እንድርያስ እንደ ወንድሙ ተናጋሪ አልነበረም፥ ነገር ግን የተግባር ሰው ነበር። የሚችለውን በማድረጉ ሊገመት የማይቻል አስተዋጽኦ አደረገ። እንድርያስ ትሁት ሰው ነበር። ስምዖንን ወደ ጌታ ያመጣው እርሱ ሆኖ ሳለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው ግን የስምዖንወንድም በመባል ነበር። ነገር ግን በዚህ ቅር የተሰኘ አይመስልም።

እንድርያስ ለሌሎች የሚገደው ሰው መሆኑን የሚያሳየን ሌላ የፈጸመው ድርጊት አለ። ይሄውም የተፈጸመው በገሊላ ባህር ዳርቻ ነበር።ሕዝቡ ቀኑን ሙሉ ኢየሱስን አልለቀቁትም። ጥያቄ ሊጠይቁት ይፈልጉ ነበር፤ ለስጋቸውም ፈውስ ይፈልጉ ነበር። ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ከሕዝቡ ግፊያ መሀል ለመውጣት ቢፈልጉም አልቻሉም። ቀኑም እየመሸ ሄደ። ከሕዝቡ አብዛኞቹ ምግብ አልበሉም። ገንዘብ ቢኖራቸውም ለዚያ ሁሉ ሕዝብ የሚበቃ የሚሸጥ ምግብ አይገኝም ነበር።

ደቀ መዛሙርቱም ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገባቸው። እንድርያስ ጥቂት እንጀራዎችና ትንሽ አሳ የያዘ አንድ ልጅ መኖሩን አስታወሰ።እንድርያስ ከልጁ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ልጁን ወደ ኢየሱስ ወሰደው። ከዚህ በኋላ የሆነውን ቀሪ ታሪክ ሁላችንም የምናውቀው ነው። ኢየሱስ የልጁን ስጦታወስዶ ባረከውና ደቀ መዛሙርትለሕዝቡ አከፋፈሉ። በርግጥ ምግቡን ስላካፈለ የሚመሰገነው ልጁ ነው። ነገር ግን ልጁን ወደ ኢየሱስ ያመጣው እንድርያስ ነበር። እንድርያስ ኢየሱስንና ልጁን አገናኘ። ከዚህም በተጨማሪ እንድርያስ ልጁን ምንም እንኳን ልጅ ቢሆንም ከኢየሱስ ጋር መገናኘትና እርሱን ማገልገል እንደሚችል አሳወቀው። ያ ልጅ ከዚህ በኋላ ምን አይነት ሰው እንደሆነ የምናውቀው ነገር ባይኖርም ከዚህ ልምምድ በኋላ ግን ከበፊቱ የተለየ ሕይወት እንደሚኖረው መገመት እንችላለን። ምናልባትም ስማቸው በአዲስ ኪዳን ካልተጠቀሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች መካከል አንዱ ይሆናል።

እንድርያስ ወንድሙን ወደ ክርስቶስ አመጣ ፤ እንጀራና አሳ ይዞ የነበረውን ወጣት ልጅ ወደ ኢየሱስ አመጣ። በተጨማሪም በዮሐንስ ወንጌል ሌላ እንድርያስ የፈጸመው ሰዎችን ከኢየሱስ ጋር የማስተዋወቅ ሥራ ያሳየናል። ይህ የተፈጸመው ኢየሱስ በምድር የነበረውን አገልግሎት ወደ መፈጸሙ በተቃረበበት ጊዜ ነበር። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ነበር። ለሐይ ማኖታቸው ቀናዒ የሆኑ አይሁዶች ከብዙ የሮም ግዛቶች ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ነበር። ከነዚህም መካከል ከግሪክ የመጡ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ግሪኮች በኢየሩሳሌም በቆዩበት ወቅት ትምህርቱንና የሰራውን ስራ ሰምተው ነበር። ከኢየሱስ ጋር ተገናኝተው ሊያነጋግሩት ወሰኑ። ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱን ማለትም ፊልጶስን አገኙትና ምን እንደሚፈልጉ ነገሩት። ፊልጶስ ምናልባት እነዚህን የውጭ አገር ሰዎች ኢየሱስን እንዲያዩት መውሰድ ያለበት ለመሆኑና ላለመሆኑ ርግጠኛ አልነበረም። ስለዚህ እንድርያስን ጠራና ጉዳዩን ገለጸለት ። እንድርያስም ግሪኮቹን ወደ ኢየሱስ ወሰዳቸው (ዮሐንስ 12፥22) እነዚያ ግሪኮች ከኢየሱስ ጋር በተገናኙበት ጊዜ በሕይወታቸው ምን እንደተፈጸመ በርግጠኝነት የምናውቀው ነገር የለም። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሆነው ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ከኢ.የሱስ ጋር መገናኘታቸው በሕይወታቸው አንድ ለውጥ ሳያመጣ የቀረ አይመስልም። እነዚህን ሰዎች ወደ ኢየሱስ ለማምጣት ኃላፊ የሆነው እንድርያስ ነበር።

እንግዲህ እንድርያስ ይህን ይመስላል። በገሊላ ባህር ዳርቻ ከምትገኝ አንዲት ትንሽ ከተማ የተገኘና ብዙም ያልታወቀ አሳ ነጋዴና ከመ ጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት መካከል ቢሆንም በመሪነት ወይም አንዳች ድንቅ ስራ በመስራት ያልታወቀ ወይም ከሌሎች ሰዎች የሚያስበልጠው ልዩ ችሎታየሌለው ነበር ። ነገር ግን እንድርያስ አስፈላጊ ሰው ነበር። ምክንያቱም የኢየሱስ የመጀመሪያው ደቀ መዝሙር ነበር። ሌሎች ኢየሱስን እንዲያዩ በመጋበዝ የታወቀ ነበር። በመጀመሪያ ወንድሙን (ከቤተሰቡ ጀመረ) ፣ ከዚያም ወጣቱን ልጅ ፤ከዚያም ግሪኮቹን።

እንድርያስ ዛሬ እኛም ራሳችንን እንድንጠይቅ ያደርገናል።እንደ እንድርያስ ደቀ መዝሙሩ ፣ ምስክሩ ፣ወንጌላዊው እንድንሆን። እኛም ምንም ተራ ሰዎች ብንሆንም ለዚህ ታላቅ ሃላፊነት መጠራታችንን መገንዘብ ይኖርብናል ። ታላላቅ ችሎታና ስጦታ ላይኖረን ይችላል። ነገር ግን እንደ እንድርያስ መሆን እንችላለን የክርስቶስ ታማኝ ተከታዮች ሆነን ቤተ ሰቦቻችንን ፣ልጆችን፣ አዋቂዎችን ወደ ክርስቶስ ስንጠራ።